በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 204264

ህዳር 30 ቀን 2014 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ብርሀኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሀኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- የኦሮሚያ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት (ኮርፖሬሽን) -አልቀረቡም

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ተሚማ ፋጂ- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ክርክሩ በገጠር መሬት ይዞታ የመጠቀም መብት ላይ ለደረሰ ጉዳት ካሳ ለማስከፈል የቀረበ ክስን መነሻ ያደረገ ሲሆን ጉዳዩ በተጀመረበት የቡኖ በደሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካች ተከሳሽ፣ የኢፌድሪ ውሃ፣ መስኖ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ ታህሳስ 12 ቀን 2012 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት ክስ በቡኖ በደሌ ዞን ጋቺ ወረዳ ዲዴሳ ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ በስሜ የተመዘገበ ስፋቱ 2.5 ሄክታር የሆነ ለውዝ እየዘራው የምጠቀምበትን ይዞታ አመልካች ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በመቆፈር የጠጠር ድንጋይ በማውጣት ይዞታው ለየትኛውም አገልግሎት እንዳይውል አድርጎብኛል፡፡ ተጠሪ ከይዞታው በየአመቱ 50 ኩንታል ምርት የማገኝ ሲሆን የአንዱ ኩንታል ዋጋ ብር 1,200 ሁኖ የተለያዩ ወጪዎች ተቀናሽ ተደርጎ የተጣራ አመታዊ ትርፍ ብር 50,000

አገኛለው፡፡ አመልካች ይህን ጥቅም ስላሳጣኝ እና በዘላቂነት ስላፈናቀለኝ የ10 ዓመት ካሳ ብር 500,000 ወጪና ኪሳራን ጨምሮ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የፕሮጀክቱ ባለቤት የውሃ መስኖ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ስለሆነ ልከሰስ አይገባም፤ ጉዳዩም ከውል ውጪ ግንኙነትን መሰረት ያደረገ ስለሆነ በፍ/ሕ/ቁጥር 2143 መሰረት በይርጋ ይታገዳል፤ የፕሮጀክቱ ባለቤትም ወደ ክሱ ጣልቃ እንዲገባ ይታዘዝልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ በፍሬ ጉዳይ ላይ በሰጠው መልስ አመልካች ከፕሮጀክቱ ባለቤት ጋር ጥር 31 ቀን 2011 እ.አ.አ. ባደረገው የአርጆ ዲዴሳ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ውል አንቀፅ 11(ኤ-1) መሰረት በፕሮጀክቱ አካባቢ ባሉ ባለይዞታዎች ላይ ለሚደርስ ጉዳት አስፈላጊውን ክፍያ ለመፈፀምም ሆነ የስራ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ኃላፊነት ያለበት የፕሮጀክቱ ባለበት ነው፤ ይዞታው ከመጀመሪያው በፕሮጀክቱ ክልል ውስጥ የሚገኝ ጥራት ላለው ድንጋይና ገረጋንቲ ምርት ተለይቶ በአማካሪ መሀንዲሱ የኦሮሚያ ውሃ ስራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት የተፈቀደ ነው፡፡ በክሱ እና በይዞታ ማረጋገጫው ላይ የተጠቀሰው የይዞታው ስፋት ልዩነት አለው፡፡ ይዞታውም ለእርሻ የማይውል ድንጋያማ እና ተራራማ ነው፡፡ ለምርት ይውላል ቢባል እንኳ በየአመቱ አንድ አይነት የለውዝ ምርት ብቻ ሊመረትበት አይችልም፡፡ ለምርታማነት የሚያስፈልጉ የምርት ግብዓት ወጪዎች በባለሞያ ሊጣራ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የውሃ መስኖ እና ኢነርጂ ሚኒስቴርም ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ታዞ በሰጠው መልስ በፕሮጀክቱ ክልል ውስጥ ለተካተቱ ይዞታዎች ተገቢውን የካሳ ክፍያ መፈጸሙን፤ አከራካሪው ይዞታ ከፕሮጀክቱ ክልል ውጪ የሚገኝ፤ አመልካች በፕሮጀክቱ ባለቤት እና አማካሪ ድርጅት ከተሰጠው ዲዛይን ውጪ በመውጣት አከራካሪውን ይዞታ ቆፍሮ ድንጋይ እና ገረጋንቲ በማውጣት ጥፋት የፈጸመ በመሆኑ ለክሱ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 59979 ቅፅ 11 ላይ እንደታተመው በዚህ መዝገብ ከተያዘው ተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የሚቀርብ ክስ በ2 ዓመት ይርጋ የማይታገድ መሆኑን ገልጾ ውሳኔ ስለሠጠ ክሱ በይርጋ አይታገድም በማለት መቃወሚያውን አልፎታል፡፡ በፍሬ ጉዳይ ላይ የግራ ቀኙን የሰነድ ማስረጃ፣ የሰው ምስክር እንዲሁም ከተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በተውጣጣ ኮሚቴ ጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት የቀረበውን ማስረጃ መዝኖ የተጠሪ ምስክሮች በይዞታው ላይ ጉዳት የደረሰ መሆኑን አስረድተዋል፤ የአመልካች ምስክሮችም የተለያዩ ምክንያቶችን ይስጡ እንጂ በተጠሪ ይዞታ ላይ ጉዳት የደረሰ መሆኑን አልደበቁም፡፡ የጋቺ ወረዳ አስተዳደር ፅ/ቤትም ከተለያዩ መስሪያ ቤት ተወካዮች ጋር በመሆን ጉዳዩን አጣርቶ ከይዞታው ላይ የሚገኘውን የምርት መጠን ግምት እንዲሁም ይዞታውን ወደ ፊት ለምርት አገልግሎት እንዲውል ለማስቻል የተከመረውን አሸዋ ለማስተካከል የሚያስፈልገውን ወጪ ገልጾ ሚያዝያ 30 ቀን 2011 በቁጥር ቲ-33/862/2011 ዓ.ም የፃፈው ደብዳቤ በተጠሪ ይዞታ ላይ ጉዳት መድረሱን አረጋግጧል፡፡ በመሆኑም አመልካች በፍ/ሕ/ቁጥር 2027(2) እና 2028 መሰረት ኃላፊነት ያለበት ሲሆን አመልካች በፕሮጀክቱ ባለቤት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ከተሰጠው የፕሮጀክቱ ክልል ውጪ በመውጣት ካሳ ባልተከፈለበት ይዞታ ላይ ጉዳት ያደረሰ ስለሆነ ጣልገብ ለክሱ ኃላፊነት የለበትም በማለት ወስኗል፡፡ የካሳ መጠኑን በሚመለከትም የተለያዩ የሚመለከታቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች የላኩትን ማስረጃ መነሻ በማድረግ በደንብ ቁጥር 135/1999 አንቀፅ 16(2,3) ተጠሪ ባለፉት 5 ዓመታት በአመት በአማካይ የሚያገኙት ብር 39,390 በ10 ተባዝቶ በድምሩ ብር 393,390፣ ውሳኔ ባረፈበት የገንዘብ መጠን ከሚሰላ ከ10 በመቶ የጠበቃ አበል እንዲሁም የዳኝነት ክፍያ ጋር አመልካች ለተጠሪ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ችሎቱም ተጠሪ በይዞታቸው ላይ በ2006 ዓ.ም ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን ገልፀው ክሱን ያቀረቡት ታህሳስ 12 ቀን 2012 ዓ.ም 2 ዓመት ካለፈ በኋላ ስለሆነ በፍ/ሕ/ቁጥር 2143 እንዲሁም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅፅ 20 በታተመው መዝገብ ቁጥር 119563 በሰጠው ውሳኔ መሰረት ክሱ በይርጋ ይታገዳል በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሮታል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው ይህን ውሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ተጠሪ ክሱን ያቀረቡት አመልካች ከ2006 ጀምሮ ይዞታቸውን ቆፍሮ ድንጋይ በማውጣት ይዞታው አገልግሎት እንዳይሰጥ በማድረግ ያፈናቀላቸው መሆኑን በመግለፅ ስለሆነ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው ከውል ውጪ ድንጋጌ ሳይሆን የህገ መንግስቱ አንቀፅ 40(8) ሁኖ ተመጣጣኝ ካሳ ሊከፈል የሚገባ ስለመሆኑ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅፅ 11 በታተመው በመ/ቁጥር 59979 ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ በፍሬ ጉዳይ ላይ የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ውሳኔ ይስጥ በማለት በነጥብ መልሶታል፡፡

አመልካች መጋቢት 7 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታውን ያቀረበው ይህን የክልሉን የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘት ባጭሩ ጉዳዩን በመጀመሪያ በተመለከተው የቡኖ በደሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የኢፌድሪ ውሃ መስኖ እና ኢነርጂ ሚስቴር በጣልቃ ገብነት የተከራካሪ በመሆኑ የክልሉ ፍርድ ቤት ጉዳን የተመለከተው በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80(3) መሰረት በውክልና ስልጣኑ ስለሆነ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን መመልከቱ ተገቢ አይደለም፤ ይዞታውም ለህዝብ አገልግሎት የዋለ ስላልሆነ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለውን የፍ/ሕ/ቁጥር 2143 በመተው ተፈጻሚነት የሌለውን ውሳኔ መነሻ በማድረግ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የይርጋ መቃወሚያውን ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ አከራክሮ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን ያለው መሆን? አለመሆኑን? ለማጣራት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልሳቸውን እንዲያቀርቡ ታዟል፡፡

ተጠሪም ግንቦት 23 ቀን 2012 ዓ.ም የተፃፈ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡ የመልሱ ይዘት ባጭሩ በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ክስ ያቀረብኩት በአመልካች ላይ ነው፤ በአመልካች ጠያቂነት ወደ ክርክሩ የገባው የስር ጣልቃ ገብ ከሃላፊነት ነፃ የተባለ በመሆኑና አመልካችም ጣልቃ ገቡ ነፃ መባሉን በመቃወም ይግባኝ ስላልጠየቀ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ ይዞታውንም ለህዝብ ጥቅም ሲባል አመልካች ለም አፈሩን ቆፍሮ በማውጣት በቋሚነት ያፈናቀለኝ ስለሆነ የአዋጅ ቁጥር 455/97፣ የህገ መንግስቱን አንቀፅ 40(8) እና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 59979 በሰጠው አስገዳጅ ትርጉም መሰረት የይርጋው መቃወሚያ ውድቅ መደረጉ ተገቢ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካችም ሰኔ 8 ቀን 2013 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልሱን ያቀረበ ሲሆን የሠበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን የመመልከቱን እንዲሁም ክሱ በይርጋ አይታገድም የመባሉን አግባብነት በስር ፍ/ቤት ከተደረጉ ክርክሮች፣ በማስረጃ ከተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች እንዲሁም ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች በዋናነት የሚከራከረው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር አይቶ የመወሰን ስልጣን የለውም፤ ለክርክሩ ተፈጻሚነት ያለው ድንጋጌም የፍ/ሕ/ቁጥር 2143 ሁኖ እያለ ክሱ በይርጋ አይታገድም ተብሎ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት ነው፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው በስር ፍርድ ቤት ክርክር ጣልቃ ገብ የነበረው ተከራካሪ ኃላፊነት የለበትም ተብሎ ስለተወሰነና አመልካች ይህን በመቃወም ያቀረበው ይግባኝ ስለሌለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ አመልካች ከይዞታው በቋሚነት ያፈናቀለኝ በመሆኑ ክሱ በይርጋ አይታገድም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

በመጀመሪያ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የመመልከቱን ተገቢነት መመርመሩ አስፈላጊ ነው፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር ተመልክቶ ውሳኔ በሰጠበት ታህሳስ 13 ቀን 2013 ዓ.ም ስራ ላይ በነበረው የፌደራል ፍርድ ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 5(1) መሰረት የፌደራል መንግስት አካል ተከራካሪ የሚሆንባቸውን ጉዳዮች የመመልከት የፍትሐ ብሔር የዳኝነት ስልጣን የፌደራል ፍርድ ቤቶች መሆኑ ተመላክቷል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ በተመለከተው የቡኖ በደሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ክስ ያቀረቡት በአመልካች ላይ ብቻ በመሆኑ ጉዳዩ ከመነሻው የክልል ጉዳይ ነበር፡፡ ነገር ግን በአመልካች ጠያቂነት የኢ.ፌ.ድ.ሪ. ውሃ መስኖ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር በክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ታዞ የክርክሩ ተሳታፊ መሆኑ ጉዳዩን በፌደራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ስር እንዲወድቅ አድርጎታል፡፡ በክርክሩ መጨረሻ ጣልቃ ገብ ለክሱ ኃላፊነት የለበትም ተብሎ ተወስኗል፡፡ አመልካች በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሲያቀርብ 2ኛ መልስ ሰጪ ተደርጎ የነበረ ቢሆንም ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታ ሲቀርብ ግን ጣልቃ ገብ የነበረው የፌደራል ተቋም በተከራካሪነት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ሳይሰየም ቀርቷል፡፡ ጉዳዩን በፌደራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር እንዲወድቅ አድርጎት የነበረው ምክንያት ማለትም የፌደራል መንግስት ተቋም የነበረው የስር ጣልቃ ገብ ከክርክሩ ውጪ መሆኑ ጉዳዩ የፌደራል መንግስት እንዲሆን ያደረገው ምክንያት ቀሪ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህም ጉዳዩ የክልል ጉዳይ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ቀደም ሲል የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 16 በታተመው በመዝገብ ቁጥር 95033 ላይ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የፌደራል መንግስት ተቋም ተከራካሪ ሳይደረግ በተጠሪ በቀረበለት የሰበር አቤቱታ ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ መወሰኑ በሌለው ስልጣን ነው የሚያስብል ሁኖ አላገኘነውም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ መፍትሔ ማግኘት ያለበት ጉዳይ በተጠሪ የቀረበው ክስ በይርጋ አይታገድም የመባሉ አግባብነት ነው፡፡ ተጠሪ ጉዳዩን በመጀመሪያ በተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክሳቸውን የመሰረቱት አመልካች ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ ስፋቱ 1.5 ሄክታር የሆነ ለውዝ እያመረቱ የሚገለገሉበትን ይዞታ ቆፍሮ ጠጠር እና ገረጋንቲ በማውጣት ለማንኛውም አገልግሎት እንዳይውል አድርጓል በሚል ነው፡፡ ተጠሪ በክሳቸው ላይ ይዞታው በኢ.ፌ.ድ.ሪ. ውሃ መስኖና እና ኢነርጂ ሚኒስቴር ባለቤትነት ለሚገነባው የአርጆ ዲዴሳ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት እንዲውል ይዞታው ሙሉ ለሙሉ ተወስዶብኛል በማለት ያቀረቡት መከራከሪያ የለም፡፡ ክሳቸው በአመልካቹ ድርጊት ይዞታው ለሌላ አገልግሎት እንዳይውል ስለተደረገ አመልካቹ ካሳ ሊከፈለኝ ይገባል የሚል ነው፡፡ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም አመልካቹ በፕሮጀክቱ ባለቤት እንዲሁም አማካሪው የኦሮሚያ ውሃ ስራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት ከተሰጠው ዲዛይን ውጪ በመውጣት የተጠሪን ይዞታ በመቆፈር ጠጠር እና ገረጋንቲ በማውጣት ጉዳት ያደረሰ መሆኑ እንዲሁም ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ላይ ትክክለኛ ውሳኔ መስጠት እንዲቻል ከተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤት በተውጣጡ ባለሞያዎች ጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በቀረበው ማስረጃ በይዞታው ላይ የተከመረውን አሸዋ በማሽን በመደልደል ለማስተካከል 7 ሰዓት እንደሚፈጅ እና ለአንድ ሰዓት ብር 3,000 ክፍያ የሚጠይቅ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህም የተጠሪ ይዞታ በፕሮጀክቱ ባለቤት ለመስኖ ግድብ ግንባታው የተወሰደባቸው አለመሆኑን እንዲሁም በአመልካች በተፈጸመው ጥፋት በይዞታው ላይ ጉዳት የደረሰ ቢሆንም በግንባታ ማሽኖች ይዞታውን በ7 ሰአታት ውስጥ እንዲስተካከል በማድረግ አገልግሎት መስጠት እንዲችል ማድረግ የሚቻል መሆኑን የሚያስገነዝብ በመሆኑ ተጠሪ ለሕዝብ አገልግሎት ሲባል ከይዞታቸው በቋሚነት አለመፈናቀላቸውን የሚያመላክት ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በፕሮጀክቱ ምክንያት ከይዞታቸው ለዘለቄታው ተፈናቅለዋል ሊባል አይችልም፡፡

ጉዳዩ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ያለን ግንኙነት መሰረት በማድረግ አመልካች ከፕሮጀክቱ ክልል ውጪ በመሔድ በይዞታቸው ላይ ያደረሰውን ጉዳት የሚመለከት ከውል ውጪ የሆነን ኃላፊነት የሚያስከትል ስለሆነ ይርጋን በተመለከተ ለክርክሩ ተገቢነት ያለው ድንጋጌ የፍ/ሕ/ቁጥር 2143 ነው፡፡ በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር 1 ስር ተበዳዩ ክስ ማቀረብ ያለበት ካሳ የሚጠይቅበት ጉዳት ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ በ2 ዓመት ውስጥ መሆን እንዳለበት ተመላክቷል፡፡ ተጠሪ አመልካቹ ይዞታቸውን በመቆፈር ጠጠር እና ገረጋንቲ ማውጣት

*ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

የጀመረው 2006 ዓ.ም መሆኑን በክሳቸው የገለጹ ሲሆን ክሱን ያቀረቡት ታህሳስ 12 ቀን 2012 ዓ.ም ድርጊቱ መፈጸሙ ከታወቀ ከ2 ዓመት በኂላ ነው፡፡

ስለዚህ በፍ/ህ/ቁጥር 2143/1 እና በተመሳሳይ ጉዳይ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅጽ 20 በታተመው በሰበር መዝገብ ቁጥር 119563 በሰጠው የህግ ትርጉም መሰረት የተጠሪ የጉዳት ካሳ ክስ በሁለት አመት ውስጥ ባለመቅረቡ በይርጋ የሚታገድ በመሆኑ ውድቅ መደረግ እያለበት ከዚህ በተቃራኒ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በቅፅ 11 የታተመውን የሰ/መ/ቁጥር 59979 በልማት ምክንያት ከይዞታቸው በቋሚነት እንዲፈናቀሉ የተደረጉ አርሶ አደሮች የሚያቀርቡት የካሳ ይከፈለኝ ክስ ላይ ተግባራዊ መደረግ ያለበትን የይርጋ ጊዜ በሚመለከት የሰጠውን የሕግ ትርጉም በዚህ መዝገብ ለተያዘው ጉዳይ ተፈጻሚ በማድረግ ክሱ በ 2 ዓመት ይርጋ አይታገድም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በአብጫ ድምፅ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. የቡኖ በደሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 03498 ሰኔ 20 ቀን 2011 ዓ.ም እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 333952 ታህሳስ 13 ቀን 2012 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሠጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 220314 ጥር 28 ቀን 2012 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት የተደረገው ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

*ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

## <u>የልዩነት ሃሳብ</u>

ሥሜ በተራ ቁጥር ሦስት ላይ የተሰየምኩት ዳኛ ከአብላጫው ሃሳብ የተለየሁበትን ምክንያት እንደሚከተለው አስፍሬያለሁ፡፡

ኢትዮጵያ የፌደራል የመንግሥት አወቃቀር ሥርዓትን በ1987 ዓ/ም በወጣው የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት መከተሏን ተከትሎ ሥልጣን በክልሎችና በፌደራል መንግሥት የተከፋፈለ ስለመሆኑ በሕገ-መንግሥቱ ከአንቀጽ 50-52 ላይ ተመልክቷል፡፡ በዚህም ክልሎች በሥልጣናቸው ሥር ባሉ ጉዳዮች ሉዓላዊ ሥልጣን አላቸው፡፡ ክልሎች እንደ ፌደራል መንግሥት ሕግ-አውጪ፣ ሕግ አስፈጻሚና የዳኝነት አካል ያደራጃሉ፡፡ በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 78 መሠረት የዳኝነት አካሉ በፌደራል እና በክልል መንግሥት ደረጃ መቋቋሙ እና በአንቀጽ 80(1)(2) ላይ በፌደራል ጉዳዮች የፌደራል ፍርድ ቤት፤ በክልላዊ ጉዳዮች የክልል ፍርድ ቤት የመጨረሻ ሥልጣን ያለው መሆኑ መመልከቱ በፌደራልና በክልል መንግሥታት መካከል የፍርድ ቤት የሥልጣን ክፍፍል እንዳለ ያሳያል፡፡ የፌደራል ወይም የክልል ጉዳዮች የሚለው በጉዳይ ዓይነት የተከፋፈለ ሥልጣን ስለሆነ የፍርድ ቤቶች ሥልጣን የተለየው የሥረ-ነገር ሥልጣንን መሠረት ያደረገ ቢመስልም ጉዳዩ ከሉዓላዊ ሥልጣን እና ክልላዊ ጉዳይ በፌደራል ፍርድ ቤት ቢታይ ከጣልቃገብነት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ጉዳዩ የብሔራዊ ዳኝነት ሥልጣንን የሚያስነሳ ነው፡፡ በፌደራል መዋቅር የብሔራዊ የዳኝነት ሥልጣን መሠረቱ ዓለምአቀፍ ሕግ ሳይሆን ሕገ-መንግሥት ነው፡፡ ሕገ-መንግሥቱ የፌደራልን ሆነ የክልልን ፍርድ ቤቶች ያቋቋመና አክብረው ለማስከበርም ግዴታ የጣለ ነው፡፡ ውጤቱም እንደ ሀገር የሚመረመረው የብሔራዊ የዳኝነት ሥልጣን ከሌላ ሀገር ዜጋ ጋር በተያያዘ እና ሌሎች ሀገሮች ጋር የዲፕሎማቲክ ቅራኔንም ሊፈጥር የሚችል ሲሆን በፌደራልና በክልል መንግሥታት መካከል ያለው ግን በአንድ ሀገር ያሉና በሕገ-መንግሥቱ የሕግ የበላይነትን በማረጋገጥ አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማሕበረሰብ ለመፍጠር በሚሠሩ ተቋማትና ዜጎች ላይ፣ የተለያየ ሥልጣን ቢሆንም የጋራ የሆኑ ጉዳዮች ደግሞ ባላቸው ተቋማት መካከል የሚነሳ ስለሆነ የተለየ ያደርገዋል፡፡ በፌደራል መዋቅር የፌደራል መንግሥት ሉዓላዊነቱ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በመላው የኢትዮጵያ ግዛት ነው። ነገር ግን በግዛቱ ሥር ሁሉንም በፈቃዱ መወሰንና መፈጸም የሚችል ሳይሆን በግልጽ በሕግ በተዘረጋው ሥርዓት ሥልጣኑን የሚጠቀም መሆኑን የሚመለከት ነው። ለክልል ፍርድ ቤት ሥልጣን መሠረቱ ግን በግዛት ክልል ሥር ያለ ሠውና ንብረት መሆን አለመሆኑን መሠረት ያደረገ (limited sovereignty) ነው።

በሕገ-መንግሥቱ የሥልጣን ክፍፍሉም የክልል ከፍተኛና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የፌደራል ጉዳዮችን በውክልና ማየት የሚችሉ ሲሆን ክልላዊ ጉዳዮች በክልሎች ሉዓላዊ ሥልጣን ክልል ውስጥ (exclusive jurisdiction of state courts) ያለ በመሆኑ፤ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80(3)(ሀ) ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት የተሠጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ማየት አይችሉም። ይሕም ክልላዊ ጉዳዮች ላይ የፌደራል ፍርድ ቤቶች የመዳኘት ሥልጣን (judicial jurisdiction) የሌላቸው መሆኑን ሲያሳይ በውክልና እና በጣምራ ሥልጣናቸው ከሚመለከቱት በሥተቀር የክልል ፍርድ ቤቶች የፌደራል ጉዳዮችን ማየት አይችሉም። ከዚህ ጋር ተያይዞ መመርመር ያለበት በሕገ-መንግሥቱ የተመለከተው የፍርድ ቤቶች የጣምራነት ሥልጣን (concurrent jurisdiction) እና የፌደራል ጉዳዮች የሚወሰኑበት ሥርዓት ነው። የፌደራል ጉዳዩች ምን እንደሆኑ በሕገ-መንግሥቱ ያልተወሰነ ቢሆንም በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 3 መሠረት የፌደራል ጉዳዮች ሕገ-መንግሥቱን፣ የፌደራል መንግሥት ሕጎችንና ዓለም አቀፍ ሥምምነቶችን መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች (based on laws)፤ በፌደራል ሕግ ተገልጸው በተወሰኑ ባለጉዳዮች (parties) እና በሕግ በተገለጹ ቦታዎች (places) ላይ የሚነሱ ጉዳዮች ናቸው። በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 4 እና 5 መሠረት የተዘረዘሩት የፌደራል ፍርድ ቤት በብቸኝነት ሥልጣኑ የሚመለከታቸው ሕግንና ባለጉዳዮችን መሠረት አድርጎ የተለዩ የፌደራል ጉዳዮች ሲሆን በሌሎች ሕጎች በግልፅ ለፌደራል ፍርድ ቤት የተሠጡ ጉዳዮችን ይጨምራል። የአዋጁን አንቀጽ 11 እና ተከታዮችን ሥንመለከት ደግሞ ቦታን መሠረት በማድረግ አዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተሞች ላይ የሚነሡ ጉዳዮች የፌደራል ፍርድ ቤት የሚመለከታቸው የፌደራል ጉዳዮች ስለመሆናቸው ተደንግጓል።

በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 3 መሠረት ሕግን መሠረት አድርጎ የተለዩት የፌደራል ጉዳዮች ውስጥ የፌደራል መንግሥት ሕጎችን መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች ያሉበት በመሆኑና በአዋጁ የትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(3) ላይ የፌደራል መንግሥት ሕጎች ማለት በሕግ በተሠጠው ሥልጣኑ ክልል ሥር ያሉ ነባር ሕጎችን የሚጨመር መሆኑ ሲታይ በሕግ በግልጽ የፌደራል ፍርድ ቤት ሥልጣን ሥር ከተመለከቱት ሕግን መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች እና በፌደራል ሥልጣን ሥር እንዲታዩ ከተወሰኑት ባለጉዳዮች ውጭ ያሉ የፌደራል ሕግን መሠረት ያደረጉ ጉዳዮች የፌደራልና የክልል ፍርድ ቤቶች በጣምራ ሥልጣናቸው የሚመለከቷቸው ናቸው። ሥለሆነም የፌደራል ሕግን መሠረት ያደረጉ ሌሎች ጉዳዮች እንደተነሱበት ቦታ የፌደራል ፍርድ ቤት ወይም የክልል ፍርድ ቤት በክልላዊ ሥልጣኑ ሊመለከተው ይችላል።

በኢትዮጵያ የፌደራል ሥርዓት መሠረት አድርጎ የተዋቀረው የዳኝነት ሥልጣን የፌደራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች ካላቸው የጣምራነት ሥልጣን ባለፈ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 78(2) እና 80(4-6) የፌደራል ፍርድ ቤት በብቸኝነት ሥልጣኑ የሚመለከታቸውን ጉዳዮች የክልል ጠቅላይና ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በውክልና እንዲመለከቱ ሥልጣን ሰጥቷል፡፡ ይህም ሕገ-መንግሥቱ የክልል ፍርድ ቤቶችን ማብቃትን (empowerment)፣ የክልሎችን ተሳትፎ ማሳደግ ላይ ዓላማ ያለውና ተቋሞቻቸው ላይ አመኔታ ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ በሕገ-መንግሥቱ የዳኝነት አካል በፌደራልና በክልል ደረጃ በየእርከኑ መዋቀሩ ሲታይ አደረጃጀቱ በተዋረድ ያለ የትይዩ አቀራረጽ (dual system) ያለው ቢሆንም የፌደራልና የክልል ጉዳይን የክልል ፍርድ ቤቶች መመልከታቸው የተደባለቀ (integrated system) እንደሚከተልም ያሳያል፡፡

የክልል ፍርድ ቤቶች በጣምራ ሥልጣናቸው በክልል ግዛታቸው የተነሱ ጉዳዮች የመመልከት ሥልጣን ያላቸው በመሆኑ የፌደራል ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አይኖረውም፡፡ ጉዳዩ በክልል ፍርድ ቤት የሚታየው ጉዳዩ የተነሳበትን ቦታና ተከራካሪውን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ የጣምራነት ሥልጣን መሠረቱ የፌደራል መንግሥት ሕግን መሠረት ያደረገ የፌደራል ጉዳይ በመሆኑ የፌደራል ፍርድ ቤት በፌደራል ጉዳይ ላይ ብሔራዊ የመዳኘት ሥልጣን የለውም ሊባል አይችልም፡፡ ነገር ግን በፌደራል ፍርድ ቤት አዋጅ ቁጥር 25/1988 አቀራረጽ መሠረት ከተለዩት ውስን የፌደራል ፍርድ ቤት ሥልጣኖች ውጭ ያሉ በክልል ግዛት የሚነሱ ጉዳዮችን የክልል ፍርድ ቤቶች እንዲመለከቷቸው የተተወ በመሆኑ ጉዳዩ የሥረ-ነገር ሥልጣን ጥያቄ የሚያስነሳ ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ የክልል ፍርድ ቤቶች በፌደራል ፍርድ ቤት በብቸኝነት እንዲታዩ የተለዩ ጉዳዮችን (exclusive jurisdiction) በግዛታቸው በተከሠቱ ጉዳዮች፣ ባሉ ሠዎች ወይም ንብረቶች ጋር የሚነሱ ሲሆን በውክልና (delegation) እንዲመለከቱ በሕገ-መንግሥት ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ የክልል ፍርድ ቤቶች በግዛታቸው ባሉ ሠዎች ወይም ንብረቶች ጋር የሚነሳ የፌደራል ጉዳይን ውክልናቸው እስካልተነሳ ድረስ የመመልከት ሥልጣን አላቸው፡፡

በዚህም መሠረት በተያዘው ጉዳይ በግራቀኙ ክርክር በሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የኢፌዴሪ ውሃ፣ መስኖ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር በክርክሩ በጣልቃገብነትና በመልስ ሰጭነት ተከራክሯል፡፡ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የፌደራል መንግሥት አካል በመሆኑ በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5(1) መሠረት ክርክሩ የፌደራል ጉዳይ ሆኗል፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክርክሩን የተመለከተውም የፌደራል ጉዳይን በውክልና የማየት ሥልጣን ያለው በመሆኑ ነው፡፡ የአመልካች ይግባኝ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከታየ በኋላ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ሊመከተው አይችልም፡፡ የክልል ሠበር ሰሚ ችሎቶች በክልላዊ ጉዳዮች ላይ የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን ያላቸው ስለመሆኑ በኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 80(3)(ለ) ላይ ተመልክቷል፡፡ የክልል ፍርድ ቤቶች በውክልና የሚመለከቷቸው ጉዳዮች የፌደራል ጉዳዮች በመሆናቸው የክልል ሠበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን አይኖረውም፡፡

ጉዳዩን የፌደራል ያደረገው ተከራካሪ በክርክሩ አለመሳተፉ ጉዳዩን መልሶ ክልላዊ ጉዳይ አያደርገውም፡፡ ጉዳዩ የፌደራል የሆነው በጉዳዩ ዓይነት ወይም በተከራካሪዎች አድራሻ ወይም በተከራካሪዎች ማንነት ቢሆንም ጉዳዩ አንዴ የፌደራል ጉዳይ ከሆነ እስከመጨረሻው በፌደራል ፍርድ ቤት ወይም የፌደራል ጉዳይን በውክልና ለመመልከት ሥልጣን ባላቸው የክልል ፍርድ ቤቶች ሊታይ የሚችል የፌደራል ጉዳይ እንጂ የውክልና ሥልጣን በሌለው ፍርድ ቤት ወይም ችሎት ሊታይ የሚችል ክልላዊ ጉዳይ ሊሆን አይችልም፡፡ ጉዳዩ የፌደራል ወይም ክልላዊ ጉዳይ መሆን አለመሆን በሕገ-መንግሥቱ ከተቀረጸው የፌደራል አወቃቀርና ከፌደራል መንግስት ሆነ ከክልሎች ሥልጣን ጋር ግንኙነት ያለው በመሆኑ አንድ ጉዳይ በፌደራል መንግሥቱ ሥልጣን ሥር ካረፈ በኋላ ተመልሶ ጉዳዩ የክልል መንግሥት ሥልጣን የሚሆንበት ሥርዓት ሊፈጠር አይችልም፡፡ ሥለሆነም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት በተጠሪ የቀረበው የሠበር አቤቱታን ለመመልከት ሥልጣን የለኝም በማለት መወሰን ሲገባው የሰበር አቤቱታውን መመልከቱ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻሩ ተጠሪ ጉዳዩ ላይ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 321(2) መሠረት በሁለተኛ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የማቅረብ መብት ያላቸው በመሆኑና ጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ያልተሰጠበት ስለሆነ በሥረ-ነገሩ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊመረመር አይገባም በማለት በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

ማ/አ                                                          የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም